

# ወያኔ ከሄደ በሁዋላ ምን ይመጣ ይሆን ?

አሚናት ኢብራሂም ከኖርዌ

የወያኔን መሄድ ተከትሎ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ባሉ ባለስልጣናት ምን ይፈጠር ይሆን? ሰራዊትስ ምን ያስብ ይሆን? ወያኔን ለማስኬድ ህዝቡ ለውጥ ለማምጣት በመጠበቅ ላይ ነው ወያኔ ከተወገደ በኃላ ሊነሳ የሚችል የብሄር ግጭት ይፈጠር ይሆን ?

ወያኔዎች ባለፉት 25 ዓመታት ለሀገር የተሻለ ሀሳብ ያላቸውን ወይም ሀገር የሚወዱትን ምሁራንና ፖለቲከኞችን በሙሉ አጭደው በልተው ጨርሰዋል ዛሬ በወያኔ ላይ የተነሳው አዲስ ትውልድ ወያኔ ስልጣን ለቆ እስካልሄደ ድረስ እስከ መጨረሻው ዋጋ ሊከፍል ቆርጦ እንደተነሳ ማረጋገጫ ማቅረብ አያስፈለገውም

ወያኔዎች ስልጣን ከያዙ ማግስት አዋቂ ናችሁ እንዲባሉ የተሻለ እውቀት ያላቸውን አባረው መተማመን የሌላቸውን በእውቀት የደከሙትን ወደኃላ ሰብስበው ስልጣን በመቆናጠጥ ህዝብንና ሀገርን ሲገድሉ ኖረዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንንና ሌሎች ተንኮሎችን በእጅጉ በመቃወም እያመፀ ይገኛል

ወያኔ በምርጫ 97 ጊዜ በአዲስ አበባ ያገኘው አጠቃላይ ድምፅ በከተማው ውስጥ ካሉ የድርጅት አባሎቹ ቁጥር አንሶ ታይቷል ይህ የሚያሳየው ወያኔን ራሳቸው አባላቶቹ እንደማይፈልጉት ነው ከጥቂቶቹ በስተቀር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ አመራሮች የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው ጊዜ የሚጠብቁ አይነት መሆናቸው ግልፅ ነው ከህዝብ እየተነሱ ላሉ ጥያቄዎች ተባባሪና ወገንተኝነት በማሳየት ላይ መሆናቸውን ታዝበናል

ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንደማንኛውም ሀገር ልዩነቶች አሉባት ወደፊትም ይኖርባታል ታዲያ በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ልዩነቶቹን ወደ አንድነት ለማምጣት የሚደረግ ሙከራ ሲሳካ ውጤት ሲያመጣ አይታይም ኢትዮጵያዊ ህብረትን የማይፈልጉ ሀይሎች አንድነትን ሁሌም ሲንድ ይታያሉ። ወያኔም ዋንኛ ፀረ ህብረት መሆኑ አይዘነጋም በሌላ አቅጣጫ ግንጠላ የሚሉትም ለአንድነት ለህብረት ዝግጁ ሁነው አይገኝም

ወያኔ በስልጣን የቆየው ህዝባዊ ድጋፍ አጊንቶ አይደለም ። ይህንንም ወያኔ እራሱ በሚገባ ያውቃል ጎጠኛ አስተሳሰብ ያለው ህዝባዊ ድጋፍ አገኛለሁ ብሎ አያስብም ዛሬ ላይ ግን ወያኔ የዘራውን ዘር የሚያጭድ በጎጥ ፖለቲካ ናላቸው ዞሮ የህዝብንም ናላ የሚያዞር ተበራክተዋል ይህ አካሄድ ድግሞ ከወያኔ ሌላ ማንንም ሊጠቅም አይችልም

የወያኔ የስልጣን መሰረት እየተናደ ባለበት ውቅት መሰረቱን መልሰው ለመገንባት የሚሯሯጡ በዘር የተደራጀ ስለ ስፍራቸው የሚያወሩ ተበራክተዋል በኦሮሞ ወገኖቻችን ስብሰባ ላይ እንደምናስታውሳቸው እንደ አቦ ሊበን ዋቆ እና ሌሎችም በሌላም ዘር ጎራ የተሰለፉ አሁን አሁን ብቅብቅ ማለት ጀምረዋል ። ነገሩን የሀገር ጉዳይ ሳይሆን ማን ከማን ያንሳል አስመሰሉት፥ ግን እንደዚህ አይነቶቹ አስተሳሰቦች ሀገራችንን ከወያኔ ውጪ እንኩዋን ወደ ለየለት የጥፋት ጎዳና እንደሚወስዳት የብዙዎች ግምት ነው ሀላፊነት የሚሰማውን ለሀገር ተቆርቋሪ የሆነ ሁሉ እጅ ለእጅ በመያያዝ ሊፋለመው የሚገባ አስተሳሰብ ነው

ሆኖም ግን ሀገራችንን ከነብስ በላው ወያኔ ለማላቀቅ ክቡን ህይወቱን እየከፈለና ከወገኑ ጋር ወንድማማችነቱን በደሙ ማህተም እያረጋገጠ ባለበት በዚህ ወቅት ከሁሉ ስፍራ የሚሰማው ጎሳ ላይ ያነጣጠረ ስብከት ለማንም አይበጅም የወያኔ በትር ቤቱን ያላንኳኩበት ኢትዮጵያዊ የለም

አንዳንድ አመለካከታቸው ችግር ያለበት የፖለቲካ መሪዎች በሚናገሯቸውና በሚሰሯቸው ስራዎች መታለል አይገባም። አሁን ያለው ግዜው እንድናስብበት እንድንነጋገርበት የወያኔን አሟሟት እንድናፋጥንበት ከዛ ባለፈ ስለ አንዲት ኢትዮጵያ የምንሰራበት ጊዜ መሆን አለበት

በህዝብ ላይ የሚፈፀሙትን ኢሰብአዊ የሆኑ የሙብት ጥሰትን የተቃወመው ህዝብ ሀገር በወያኔ ሲቸበቸብ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያዊያን ነች ብለው የተቃወሙትን የእምነት ነፃነታችንን አናስነካም ብለው በሰላማዊ መንገድ ሙብታቸውን የጠየቁና በሌላም ሀገራዊ ጉዳይ ላይ እንደ ዜጋ ይመለከተናል ያሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይ የተማረውንና ወጣቱን ስም እያወጡ እየገደሉ በየመሳሪያው በእስር መማሰቃየት ገሚሱንም በማሳደድ ኢትዮጵያ የምንላትን የሁላችን የሆነች ሀገር የአንድ ጎሳ ቡድን የግል ሀብት አድርገዋታል

ለዚህ ሁሉ በሀገርና በህዝብ ላይ ለሚደርሰው እንግልት መዋከብ ምንም እንኩዋን የመንግስትን እርካብ የተቆናጠጡት ገዥዎች ከተፈጥሮ ባህሪያቸው አንፃር የፈለጉትን ያሻቸውን ቢያደርጉም በየጊዜው በህዝብ ላይ የሚያደርሱትን ሰቆቃ የየሰሞኑ መነጋገሪያ ከማድረግ በዘለለ ህዝብ እንደ ህዝብ በደል በቃኝ ግፍ፣ መታሰር፣ መገደል በቃኝ ከሃብትና ከቀዬ መፈናቀል በቃኝ ብሎ በተለይ በሀገር ቤት ያለው የበደሉ ገፈት ቀማሽ የሆነው ወገን ለለውጥ ጥግ ድረስ ከወያኔ ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቆ በሚገኝበት ሰኣት በውጭ የሚገኘው ዲያስፖራ በጎሳ በዘር ተከፋፍሎ ትግሉን ለማዳከም ሲጥር ይስተዋላል

ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያኖች እንደሆነች መዘንጋት የለበትም ጥቂት ዘረኛ ቡድኖች ወያኔ ሮል ሞዴል የሆናቸው ሆድ አደሮች እነርሱ በሰው ሀገር የቅንጦት ኑሮ እየኖሩ ብዙሃኑ አጥንቱን ከስክሶ ደሙን አፍስሶ ባቆያት ሀገር ላይ ቁማር መቆመር ጀምረዋል

እናም ዘረኛው የወያኔ ስርዓት እንዲያበቃለት እነርሱም ከተሳሳተ አስተሳሰባቸው መውጣት የግድ ነው። እኛ እልፍ አእላፍ ነን ለነፃነታችን፣ ለሀገራችን አንድነት ለወደቀው ክብራችን በአንድነት እንነሳ ኢትዮጵያ የኛ የብዙኃን እንጂ የጥቂት ዘረኛ ቡድን መፈንጫ አትሆንም!!!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!